# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## የእውነት ብዕር ታጠፈች፥ የሃቅ አንደበት ተዘጋች፥ ኢትዮጵያ አንድ ግዙፍ የማንነቷን ነፀብራቅና የክፉ ቀን ጠበቃ ልጇን አጣች፤

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በሊቅ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ-መድኅን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የተሰማውን መሪር ሐዘን ሲገልጽ በከፍተኛ የእጦት ስሜት ነው።

የእኝህ ታላቅ ሊቅ አንደበት፥ ብእርና ሰብእና ሁሉ እስከ ዕለተ እረፍታቸው ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዬ ከማለትና እውነትን፥ በእራስ መተማመንን፥ ኩራትን ትህትናን፥ ፍቅርንና አንድነትን ከመግለጽና ከማስተማር ላፍታም እንኳን ቦዝነው አያውቁም። መንፈሰ-ጠንካራና አቋመ-ብርቱ የነበሩት ሊቅ ፀጋዬ ገብረ-መድኅን የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ምንነትና ማንነት መግለጫ፥ ቋሚ ሰነድ፥ ተንቀሳቃሽ ቅርስ፥ ዋቢና ጠበቃ፥ አለኝታና የኢትዮጵያዊ አርቆ አስተዋይነት ተምሳሌት ነበሩ።

ከልብ የሚወዷት አገራቸውና እጅግ በጣም የሚያፈቅሩት ወገናቸቸው ኋላ-ቀር አገዛዞች ለወለዷቸው ለማያባራ የፍትኅ መጓደል፥ ለሰው-ሰራሽ አሳፋሪ ችጋርና ጠኔ፥ ለበሽታ፥ ለሰላም ማጣት፥ ለመከፋፈል፥ ወዘተ... በመዳረጋቸው ልባቸው እንዳዘነና እንደተከዘ፥ በአንጻሩ ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ባላቸው ሙሉ እምነት ይዋል ይደር እንጅ ሕዝቡ አንድነቱን ጠብቆ፥ ችግሩን በጋራ ተቋቁሞና ተወጥቶ አገራችን ለዳግም ትንሳዔ እንደምትበቃ ሙሉ ተስፋ እንዳላቸው ግልጽ ነበር።

ሊቅ ፀጋዬ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ምሥረታ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት ድርጅቶቹን በመመምከርና በማበረታት ለኅብረቱ ምሥረታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ታላቅ ሰው ነበሩ። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ከተመሠረተ በኋላም የኅብረቱ የብሔራዊ አማካሪ ምክር ቤት አባል በመሆን፥ ኅብረቱ በተመሰረተበት መንፈስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሥልጣኑ ባለቤት መሆን የሚያስችለው ፍትኃዊ ሥርዓት አስገኝቶ ትግሉን በመቻቻልና በጠነከረ አገራዊ ስሜት እንዲቀጥል ቀጥተኛና ግልጽ ምክሮቻቸውን በጉባዔዎቻችን ላይ በአካል በመገኘት ለግሰዋል፥ በኅብረቱ ውስጥ የተነሱ ልዩነቶችን ለማስወገድ በቀና መንፈስና በቀጥተኛነት ከልብ ጥረት አድርገዋል። ለአገራችን ኢትዮጵያና ለሕዝቧ በጎ የሚያልሙና የሚመኙ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ድርጅቶች ሲያብሩና በጋራ ሲቆሙ ልባዊ ደስታ ተሰምቷቸዋል፥ ልዩነት ሲፈጠር ደግሞ ልባቸው አዝኗል።

አገራችን ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ሊቃውንት አንዱ የሆኑት ተመራማሪና ምሁር ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድኅን መሰልና ምትክ የማይገኝላቸው ብርቅና ድንቅ ጥሪታችን ነበሩ። እኝህ ሊቅ የአስተሳሰባቸው አድማስ በጣም ሰፊና ከኢትዮጵያም አልፎ በአፍሪቃዊነት፥ ከዚያም አልፎ በሰው ዘር አባልነት ላይ ያማከለ ስለነበር በዘመናችን ዜጎችን በቋንቋና በጎሣ የሚከፋፍል ኋላ-ቀር ሥርዓትን አጥብቀው ይጠሉት፥ ይንቁትና ያዝኑበት የነበር ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን የመሠረተው የተቃዋሚዎች ሁሉን-አቀፍ አገራዊ ጉባዔ ላይ ተገኝተው ካስተላለፉት መልእክት ውስጥ የሚከተለው ይገኛል፥-

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

“ ክቡራትና ክቡራን የኅብረት ጉባዔተኞች፤ ቶሎ  ተባበሩና ተንቀሳቀሱ:: ዛሬ ታላቁ ታሪካዊ አጀንጋችሁ÷ የሞት የሽረት አንገብጋቢ አጀንጋዳችሁ÷ እናት አገራችንን ከመቀመቅ ጉድጓድ አፍ የማዳን አጀንዳ ነው:: ወደፊት በውይይት ልትፈቱት በምትችሉት በጥቃቅን ልዩነቶቻችሁ ላይ ዛሬ በመነታረክ÷ የኅብረት ሰዓታችሁ ከእጃችሁ ካመለጠ ግን ገዥው ክፍል አገር የመግደል አጀንዳውን አቀላጥፎ አከናውኖ÷ የታሪክ እድፉን በእናንተው የመተባበር ብቃት ማነስ ላይ አላክኮ እንዲያጠናቅቅ÷ ጊዜውንና ዕድሉን እያወቃችሁ ሰጣችሁት ማለት ነው::እናንተንም እራሳችሁን÷ አስቀድሞውኑ ወደቆፈረላችሁ ጉድጓድ አውርዶ÷ አፈር እንዲመልስባችሁ ጊዜውንና ዕድሉን ሰጣችሁት ማለት ነው:: … ሞት በሕይወት ለተወለደ የዓለም ፍጥረት በሙሉ የመጨረሻ ፅዋው ነው:: ታሪካዊ ሞት ግን ለሰማዕታት የተመደበ የአባቶቻችሁ ታሪካዊ ፅዋ ነው:: ፅዋውን አትፍሩት:: … ለአገር÷ ለወገን መሞት የክብር ሞት …. ነው::  ዓለም ያደነቀው የአባቶቻችሁ ታሪክና ባህል ታንፆ የቆያችሁ በመተማመን ፅኑ መሠረት ላይ ነው:: ኢትዮጵያዊነትና የመተማመን ባህል ከቶም ተለያይተው አይታዩም:: ካልተማመናችሁ በስተቀር እውነተኛ ኅብረት እንደማይገኝ ሁሉ÷ ያለኅብረት ደግሞ እውነተኛ ድል አይገኝም::”

ሎሬት ፀጋዬ ወደሚወዷት አገራቸው በሕይዎት ተመልሰው በሚያከብሩትና በሚያፈቅሩት ወገናቸው መኻል በአካል ተገኝተው የአንድነት÷ የእኩልነት÷ የፍትኅ መልእክቶቻቸውን ማስተላለፍና ማስተማር አለመቻላቸውና ወገኖቻቸውም ዕድሉን ማግኘት አለመብቃታቸው ያሳዝናል::

ስም ከመቃብር በላይ ነውና የብእር ብቻ ሳይሆን የእውነትና የአንድነት አርበኛ የነበሩት ሊቅ ፀጋዬ ገብረ-መድኅን ዕድሜ ልካቸውን በለገሱን የኪነትና የሥነ-ጥበብ ሥራዎቻቸው ወገናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብና አገራቸው ምን ጊዜም ሲዘክሯቸው ይኖራሉ÷ በሥራዎቻቸው ኅያው ናቸውና::

የእኝህ ውድ ዜጋ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ሃዘን የመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆንም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ለሎሬት ፀጋዬ ባለቤት÷ ልጆችና ቤተሰብ መጽናናትንና ብርታትን እንዲሰጥ ከልብ እንመኛለን::

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም